# ስለ አበበ በቂላ የህይዎት ታሪክ ሙቪ

## የግል ትዝታና አስተያየት

**በዘውገ ፋንታ**

ስያትል 2010 zegfantam@aol.com

በቅርቡ የአበበ በቂላን ታሪክ ***"ዚ አትሌት"*** የተባለውን ሙቪ ስላየሁ፣ አንድ ጊዜ የኖርኩበትን ሀገር ኢንግላንድን አስታውሶኛል። ከብዙ ዓመቶች በኋላ እየተረሳኝና እየተዘነጋኝ የሄደውን ትዝታ እንደገና አድሶታል። ኢንግላንድ በትምህርት እያለሁ፣ አበበ በቂላ ታሞ ከተኛበት ሆስፒታል ተጉዤ ጠይቄው ነበር። አበበ ከተኛበት ክፉል ውስጥ ያየሁትን፣ ምን ጊዜም የማይረሳኝን ገጹን በሙቪው ውስጥ እሱን ተመስሎ የሰራው አክተሩ ስሜት በሚቀሰቅስ መልክ አስታውሶኛል።

በአምሮየ ተቀርጾ የኖረውን የአበበን የዚያች ቀን መልኩን በሚገባ ቁልጭ አርጎት ነበር። ረጅም ፊቱን፣ ችፍግ ያለው ጺሙን፣ ትራሱ በጣም ቀጥ ያለው አልጋው፣ የአበባዎቹ ብዛት፣ የከረሚላውና የብስኩቱ ፓኮዎች ክምር፣ በይበልጥም ደግሞ ከጃፓን፣ ጣሊያን፣ አሜሪካ፣ ሜክሲኮ፣ ኢትዮጵያና ከዓለም ዙሪያ የተላኩለት ደብዳቤች የታሸጉበት ሳጥኖች ቁልልና ከነገሥታት፣ ከፍተኛ ባለሥልጣኖችና የሀገር መሪዎች የተላኩት ደብዳቤዎች ተከፍተው በጎኑ ተከምረው ያየኋቸውን ሁሉ ሙቪው ትዝ አሰኘኝ።

ሙቪውን ያዘጋጀው እጅግ ሰፊ ጥናት እንዳደረገ ግልጽ ነበር። ለአበበ የተላኩትን ከፊል ፖስታዎችን የያዘ በጥግ ተቀምጦ ያየሁት አንድ ኬሻ በሙቪው ላይ ምስሉን ኬሻ አይቸ ተደንቄአለሁ። በሙቪው ላይ ኬሻ ሳይ፣ ለሙቪው የተደረገውን የጠራ ጥናትና ጥንቃቄ በአድናቆት ተገንዝቤአለሁ። ታሪኩ እንደነበረ አድርጎ ለማቅረብ አዘጋጁ የተጠናቀቀ ሰፊ ጥናት ማድረጉን ሙቪው ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ጎልቶ ወይም አንሶ የቀረበ አላየሁም። ይኼም የአዘጋጁን ጥልቅ ሙያና የሙቪው ታሪክ አቀራረብ መለኪያ መሆኑን በመገንዘብ ስለ ጥራቱ የግል አድናቆቴን እገልጻለሁ።

አንድ ሌላ አስደናቂ ሙቪ ስለ አበበ ታሪክ በብዛት የሚያሳይ፣ በአንድ የታወቀ ጃፓናዊ ሙቪ አዘጋጅ የተሰራ አይቸ ነበር። 70 ሚ/ሜ ስክሪን ባለው ሲኒማ ቤት ብቻ ነበር ሊታይ የሚችለው። ሙቪውን ከአዘጋጁ ጋር ተጻጽፌ ከብዙ ጥረት በኋላ በዛ ያለ ገንዘብ ከፍየ ስያትል አስመጥቸ በ80's ዓመቶች መጨረሻ ላይ ለኢትዮጵያኖችና ለኗሪው ስፖርት አፍቃሪዎች አሳይቸው ነበር። ያ በዓለም ዙሪያ የታየው ሙቪ እስከአሁን ድረስ በኢትዮጵያኖች አይን አበበ በቂላን አስመልክቶ እጅግ ግሩም እየተባለና እየተደነቀ ቆይቷል።

ዛሬ ያየሁት አስደናቂ ሙቪ የአበበን ሙሉ ታሪክ በሞላ ጎደል ያዘለ በማናቸውም ረገድ ወደር የማይገኝለት ዶኩመንታሪ / ሙቪ ነው ብዬ በመመስከር ብናገር ድፍረት እንዳልሆነ እተማመናለሁ። ሙቪውን አይቶ በስሜት የማይነካ ኢትዮጵያዊ ይኖራል ብየ አላምንም። ማሞ ወልዴንም በህይዎት አግኝቸው ነበር። ከሱ ጋር የቪዲዎ ኢንተርቪው አዘጋጅቸ ስለ እራሱና ስለ አበበ በቂላ የተናገረውን ቀርጨ አስቀምጨዋለሁ። ማሞ ወልዴ ስለ አበበ የተናገረው፣ የኢትዮጵያውያንነትን ታላቅ ባሕሪ የሚያሳይ ነው ብዬ አምናለሁ። ማሞ ስለ ወዳጁ ታላቅ ክብር እንጂ ስለ ራሱ ተደጋግሞ ሲጠየቅ እንኳ የሰጠው ወይም የሚሰጠው መልስ ዞሮ ተመልሶ ስለ ወዳጁ ስለ አበበ ታላቅነት ነበር።

ከአበበ በቂላ ጋር ከሆስፒታሉ የተነሳኋቸው ፎሮግራፎች ካሜራውንና ፊልሞቹን የያዝኩበትን ቦርሳ በባቡር ስጓዝ ከጎኔ አስቀምጨው ስለነበር፣ በምወርድበት ጊዜ በትካሻየ ያነገትኩትን ብቻ ጨምድጄ ይዤ ሌላውን ረስቸ ወጣሁ።

ቆይቸ ሳስታውስ ባቡሩ ከመቅጽበት መንደሩን ሰንጥቆ ሄዷል። ለባቡሩ ሰራተኞች እንዲያፈላልጉና ዕቃውን ላገኘው ሰው ካሳ የሚሆን ብዙ ገንዘብ ሰጥቸ ነበር። ያገኘው ሰው ይመልስልኛል በሚል ተስፋ ብዙ ሳምንቶች ከዚያም ወሮች አለፉ። ዕቃዬ እንዲመለስ ይህ ሙቪ አዲስ ተስፋ አሳድሮብኛል ብል፣ አንዳንድ አንባቢዎች 'እብድነት' ቢሉት አላዝንም። ልቤ እንደ ዱሮው ነው።

ስለ አበበ በቂላ የዚህ አይነት ሙቪ በወገኖቼ ተዘጋጅቶና በላቀ ጥበብ ተሰርቶ በህይወቴ አያለሁ የሚል ህልም አልነበረኝም። ኢትዮጵያኖችን ያቆይ እንጂ ገና ብዙ እናያለን ለማለት በቅተናል። የሚመጣው ትውልድ ታላቅ ዕድል ሰምሮ ይጠብቀዋል የሚል ተስፋ ክበናል። ከሆነ መጪው ትውልድ ከዚህ ከኛ ትውልድ በበለጠ ታሪካችንን ያሳምሩታል ብየ አምናለሁ። በቅርቡ ፕ/ር ኃይሌ ገሪማ ያዘጋጀውን *"ጤዛ"* የተባለ ሙቪ አይቸ ከመደሰቴም በላይ ኢትዮጵያኖች አዲስ ነገር ለማፍለቅና ለመፍጠር ያላቸውን ስጦታና ችሎታ ስለተረዳሁ እጅግ ተደንቄአለሁ። በችግር ወቅታችን ጊዜ እየረሳን ነው እንጂ፣ መለስ ብለን ታሪካችንን ከተመለከትን ግን ምን ጊዜም እንዲህ ነበርን። የራስሴላስን እና የሀይሌን ሙቪዎች አይቸ ኩራቴና ተስፋየ ሰማይ መጥቋል ብል ትክክለኛው ስሜት ነው።

ለንዶን እያለሁ፣ የአለማየሁ ቴዎድሮስን ፎቶግራፍ አጽሙ ከተቀመጠበት የነገሥታት መቃብር ውስጥ አይቸ ልፈይመው ያልቻልኩት የተፈራረቀ ንዴትና የደስታ ስሜት አደረብኝ። ከዚያም ስለደረሰበት ስደት በመደነቅና በመገረም ታሪኩን እየፈለኩና እየተከታተልኩ አነብ ጀመር። በህጻንነቱ ከማያውቀው ዓለም ለስደት ተዳርጎ እስከ ሞተበት ቀን ድረስ ሲኖር የደረሰበትን ጭንቀትና ብቸኝነት በማሰላሰል ብዙ ጊዜ አሳልፌአለሁ። እንጀራ፣ ስጋና ሽሮ ወጥ፣ ቆሎና ዳቦው እንዲሁም ሰውንና ሀገሩን ጭምር በጣም እየናፈቀ እንደኖረና አምሮትም እንደሞተ እየገመትኩ አዝን ነበር። በኔ ጊዜ እንደአሁን ብዙ የኢትዮጵያ ምግብ ቤቶች ባይኖሩም፣ ከኢትዮጵያ እየተላከልን በየቤቱ ተሰብስበን ዶሮ ወጡን እንበላ ነበር። ምናልባት በወር ሁለትና ሶስት ጊዜ አለበለዚያ አንድ ጊዜ አይቀርም ነበር። ስለዚህ በሰው ፍቅርና በምግብ ናፍቆት እንደ አለማየሁ አልተጠቃንም። አለማየሁን ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ተገናኝተው አጫውቱት የሚል ካነበብኳቸው ታሪኮቹ ውስጥ አላየሁም። ከቦታ ቦታ በሞግዚትነት ከያዙት ቤተሰቦች ጋር በየሀገሩ ተጉዟል። የክረምቱ ቅዝቃዜ እንዳሰቃየው ተረድቻለሁ። በኑሮው አንድም የጣመው ነገር እንዳላገኘ ግልጽ ነበር። የአለማየሁ ቴዎድሮስ አሳዛኝ ታሪክ የገሀነም ቂጥ ነበር ብል ማጋነን አይሆንም ብዬ እገምታለሁ። ያስደስታውና በመልካም ያሳለፈው አንድም ደቂቃ እንዳልነበረ ካነበብኩት ታሪክ ልረዳ ችያለሁ። በብቸኝነትና በሀዘን ተውጦ ያሳለፈውን ሰፊ ጊዜ ግን መገመት ይቻል ይሆናል ወይም አይቻልም። እኔ ወደ ውድ ሀገሬ ተመልሸ ሁሉንም ናፍቆቴን ለመወጣት ዕድል ሳገኝ፣ ኢትዮጵያን አንድ ያደረገው የአፄ ቴዎድሮስ ልጅ ግን በግዞት ኖሮ አባቱ በገነቡት ሀገር ለመቀበር እንኳን ዕድል አላገኘም። በነገሥታት መካከል ያለውን ትልቅ ፎቶግራፍ ፊት ለፊት ቆሜ ሳስተውል፣ አለማየሁ ከተኛበት ቀጥ ብሎ፣ "ይህ ቦታየ አይደለም፤ አንሱና ከከብት እረኞች ጓደኞቸ መቃብር መካከል አስቀምጡኝ። ከቻላችሁ ግን ከእናቴና አባቴ አጽም መካከል አስቀምጡኝና ለዘላለም ልረፍ" ብሎ የሚለምን ይመስላል። አጽሙ ከእናቱና ከአባቱ ጎን የሚያርፍበት ቀን እንዲመጣ ህሊናችንን የሚወቅስ ታሪክ እየጮኸ ነው ብየ አምናለሁ። የአለማየሁ ታሪክ ሙቪ አዘጋጆችን ይጠብቃል። ሙቪ አዘጋጆች ቁጥራቸውን ያብዛው፤ ያሉትንም ሌላ መቶ ዓመት ያቆያቸው።

አበበ በቂላ በህክምና እያለ ሀገሩን እንዴት እንደናፈቀ ከአነጋገሩ ግልጽ ነበር። ያ ጀግና ኢትዮጵያዊ ብቻውን ሆስፒታል ብዙ ጊዜ ማሳለፉ፣ የሰው ልጅ የወጣውን ታላቅ ሽቅበትና የወረደበትን ቁልቁለት በሰው ልጅ የሚደርሰውን ጉድለትና ዕክል ሁሉ ታሪክ ያስተምረናል። የነ አፄ ልብነ ድንግል፣ አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ዮሐንስ፣ አፄ ኃይለሥላሴ የሌሎችም ንዑሳን ሰዎች ታሪኮች ጎልተው የሚታዩ ምሳሌዎች ሲሆኑ፣ ግን የሰው ልጅ ደግሞ ደጋግሞ ለሚፈጽመው ልምድ ማገጃ አልሆኑም። በሌላ አንጻር ደግሞ ሳይታሰብ በኑሮ የሚደርሱት ከባድ ዕክሎች ሰው መሆናችንን እንድንገነዘብ ያደርገናል። አበበን በአልጋው ላይ ተለጥፎ ሳየው አዕምሮዬ ምን እንደጠበቀ አላውቅም ደንገጥኩ። ጂሙ ግርማ ሞገስ የተጎናጸፈ የባህታዊ መልክ ቢመስለኝም በፎቶግራፍ የማውቀው ያ የስፖርት ሰው ሆኖ አላገኘሁትም። እንደውም ጂሙን የሚቆርጠው ሰው ያጣ መስሎኛል። ግን ግርማ ሞገስ ሰጥቶታል። እሱን ለማየትና ለመጎብኘት የሚመጣው ሰው ቁጥር ልክ እንደሌለው ተነግሮኝ ነበር። ሙቪው ካስታወሰኝ ብዙ ነገሮች አንዱ በውጭ ያነጋገርኳት ነርስ ነበረች። ስለ እኔ የጠየቀችውና የወሰደችው ግምት ስህተት

ነበር። ኢትዮጵያኖች አበበን ለመጠየቅ ሲመጡ ሰተት ብለው እንዲገቡ የተፈቀደና የታዘዘ መስሎኛል። ስለሆነም መሰለኝ እንደደረስኩ ቶሎ ሰተት ብየ የገባሁ። አበበም እጁን ዘርጋ በማድረግ ፈገግ ብሎ ተቀበለኝ። መጀመሪያ ሳየው ክው ብዬ ነበር። ግን ቶሎ ሳቅና ፈገግ ብሎ ባላየው፣ ተሸፋፍኖ ወይም አይኑን ጨፍኖ ባገኘው ኖሮ እስከአሁን የያዝኩት ትዝታ አይፈጠርም ነበር። ቶሎ ብሎ እንደምነህ አለና ና ወይም ነይ ብሎ እጄን ያዘ። የሚናገር አልመሰለኝም ነበር። እግዜር ይቅር ይበለኝ እንጂ ናቅ ያደርገኛል የሚልም ግምት ነበረኝ። እኔ አንድ ቅንጣት ልጅ፣ እሱ የዓለም ንጉሥ፣ እንደሚገባው ያን ጊዜም አሁንም ቢሆን አምናለሁ። ለአባቴና ለዘመዶቸና ለትላልቅ ሰዎች እንዳደረኩት ሁሉ ማለት ነው። አበበንም እግሩን ብስም ተገቢ ነበር። ዳሩ ግን ለትንሽ ጊዜም ብትሆን እንደ ልጁ ሆኘ መታየቴ እስከ አሁን ድረስ ያልጠገብኩት ስሜት ነው። አንድም ቃል አልተናገርኩም። ግን ከጎኑ ቁሜ አይን አይኑን አየው ነበር። አማረኛ መናገሩ፣ ወይም የሚናገረው ሰው ሲያገኝ ደስ ይለው ነበር ብዬ ክሁኔታው ገምቻለሁ። ከሌሎች ጋር ንግግሩ በእንግሊዝኛ አጭር "የስ፣ ኖ" እንደነበር ተሰምቶኛል። ዝም ስላልኩ ሊፈትሸኝ እንደሆነ አላውቅም፣ እጁን ወደ አንድ ደብዳቤ አመልክቶ እስቲ ያንን አንብቢ ወይም አንብብ አለኝ። ልሰማ የፈለግሁት "አንብቢ" የሚለውን ቃል ነበር። ያን ጊዜ በትክክል ባልሰማውም በኋላ የፈለኩት ሆኗል። ከጎኑ ቁሜ ደብዳቤ እያነበብኩለት ሳለሁ፣ አንድ ሀሳብ በአዕምሮየ እንደመጣ ትዝ ይለኛል። እሱም፣ ኢትዮጵያ ያሉት ጓደኞቼ ሁሉ ከአበበ ጎን ቆሜ እንዲያዩኝ ያደረብኝ ምኞት ነበር። እንዳጋጣሚ ያ ምኞቴ ለዘላለም ሳይሳካ ቀረ። በጺሙ ምክንያት አበበ የማውቀውን አቤን አልመስል እያለኝ ሀሳቡ በአእምሮየ ተመላለሰ። እሱ መሆኑን መጠራጠሪ አልነበረም። ምናልባት በደምብ ያጠናሁት ገጹ እንዳለ ሆኖ ስላልጠበቀኝ ነበር ብየ ገምቻለሁ። ዳሩ ግን፣ ከዚያም በፊት በህይወቴ አበበን ቀረብ ብየ አይቸው ስለማላውቅ ያም ተጨምሮበት እንደሆነ እየቆየ ተሰማኝ። ይህ ሁሉ ሆኖ፣ ግርማ ሞገሱ በአንድ ፊቱ ላይ ሁለት የንጉሥና የጳጳስ ገጾች ታይተውኛል። ይህ ደግሞ፣ ያን ጊዜ በርግጥ የተሰማኝ እንጂ አሁን ያሰብኩት አይደለም።

ባዝ ከተባለችው ከተማ የጃንሆይን የስደት መኖሪያ ቤት ጎብኝቸ ነበር። አንድ ትልቅ ሴት ስታስጎበኘኝ፣ የጃንሆይን አትክልት መናፈሻ ቦታ የነበረውን አሳየችኝ። ማዳም ቱሶድ የሰራችው አንድ በነጭ ኖራ የተሰራ የጃንሆይ ጉርድ ሀውልታቸውን በአበባው መካከል ከረጅም ድንጋይ (እንጨትም ይሆናል) ላይ ተቀምጦ አየሁ። ጃንሆይ ቁጭ ብለው መጽሐፍ እያነበቡ ያሳልፉበትን ቦታም አሳዩኝ። በዚያ ቦታ የግዞቱ ዓመታቸውን እንዴት እንዳሳለፉ የሚገልጽ አጭር ታሪክ ተጽፎ ያየሁ ወይም አንድ ጽሑፍ ተሰጥቶኝ አንብቤ ይሆናል ታሪኩን አስታውሳለሁ። ጃንሆይ ያሳለፉአቸውን የግዞት ዓመቶች ከዚያች ቦታ ቆሜ አካባቢውን እያየሁ ትንሽ እያሰላሰልኩ ቆየሁ። እንግላንድ ለብዙ የኢትዮጵያ ታሪክ መነገሪያ ወይም ሙቪ ማዘጋጃ ቦታ ትሆናለች ብዬ አምናለሁ።

አበበ ለኢትዮጵያ የሺ ዓመት መኩሪያና መከበሪያ ታሪክ በእግዜር ፍቃድ ስለሰራሁ ከእንግዲህ በኋላ የምመኘው ነገር የለም ብሎ ነበር። አበበ ለኢትዮጵያ የሺ ዓመት ታሪክ ሰጠ፤ እኛ ግን አስተማማኝ አምስት ዓመት ልንሰጣት ከማንችልበት ደረጃ ነን።

ማንም ኢትዮጵያዊ ይህንን ሙቪና የሀይሌ ገሪማን ሙቪዎች ማየት ይገባዋል ብዬ አምናለሁ። እነዚህ ሙቪዎች በአንድ ከተማ ሲታዩ ወገን እንዳያመልጠው ሩቅ ቦታም ቢሆን ተጉዞ ማየት አለበት። እንደውም፣ ቤተሰቡንና ማናቸውንም ሰው ጎትቶ በመውሰድ እንዲያይ ቢያደርግ፣ ከምንም የበለጠ ስጦታ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ። ራስሴላስን እና ሀይሌን ይባርካቸው። ያገዙአቸውና የተባበሩአቸው እንዲሁም እነዚህን ታሪካዊ ድርጊቶች ለመፈጸም እንደነሱ የደከሙትን ሁሉ ሰፊ ጸጋ ይስጣቸው። በሙቪው የተደሰትኩና የኮራሁ አንድ ወገን አዘጋጆቹን ከልብ አመሰግናለሁ።

በአርዕስቱ ላይ እንዳመለከትኩት፣ ይህ ጽሑፍ የግል ትዝታና አስተያየት እንዲሆን ፍላጎቴ ስለነበረ ያንን ያደረኩ መሆኔን ጠቅሸ እደመድማለሁ።